# የኢትዮ-ሼፕ (SHEP) የተግባር እውቀት መመዘኛ መጠይቅ (መልስ ያለው)

**ዞን................................ ወረዳ..............................ቀን.................................**

ትክክለኛዉን መልስ የያዘውን ቁጥር ከምርጫው ፊት ለፊት ባላው ክፍት ቦታ ይሙሉ

| ተ/ቁ | ጥያቄ | ምርጫዎች | መ | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የሼፕ አቀራረብ ምንድን ነው? | 1. በምርምር ላይ የተመሰረተ የማስፋፊያ አቀራረብ<br>2. ኤክስፖርት ላይ ያተኮረ የኢንዱስትሪ አቀራረብ<br>3. ከላይ ወደ ታች አቀራረብ<br>4. ገበያ ተኮር አቀራረብ | 4 | ሼፕ-ገበያ በአነስተኛ ማሳ ላይ ለሚሰሩ አርሶ አደሮች ገበያ ተኮር የግብርና ኤክስቴንሽን ስልት/ አቀራረብ ነው።በአርሶ አደሮች መካከል የገበያ መረጃ እንዲደር በማድረግ ግብርናን እንደንግድ እንዲመለከቱት ማስቻል ነው።<br>እንዲሁም በተጓዳኝ አርሶ አደሮችን የሚያነቃቁ ተግባራት ይከናወናሉ። |
| 2 | የሼፕ ዋና ዋና ንድፈ ሀሳቦች ሁለት ጽንሰ ሀሳቦችን ይይዛሉ። አንደኛው የኢኮኖሚ ንድፈ ሀሳብን ሚመለከተው ‹‹ያልተመጣጠነ የመረጃ ዘዴን የያዘ ገበያ›› ሲሆን ሁለተኛው ምንድን ነው? | 1. የስነልቦና የማነሳሳት ንድፈ ሀሳብ<br>2. የኬሚስትሪ የማስፋፊያ ንድፈ ሀሳብ<br>3. የአለም አቀፍ ዕድገት የወደፊት እድሎች ንድፈ ሀሳብ<br>4. የኑጌ የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ንድፈ ሀሳብ | 1 | መልሱ የስነ-ልቦና ንድፈ ሀሳብ ሲሆን ይህም በራስ መወሰን፤እችላለሁ የሚል ስሜትና፤ከሌሎች ጋር ተዛማጅነትን ስለሚያካትት ሰዎችን ያነቃቃል |
| 3 | ከሚከተሉት መካከል ‹‹የሼፕ አራቱ ወሳኝ ደረጃዎች›› ትክክለኛው የተግባሮች ቅደም ተከተል የትኛው ነው? (ማስታወሻ፡ እዚህ ላይ የተዘረዘሩት ከተግባሮቹ መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው) | 1. (1) የገበያ ጥናት ማካሄድ፣ (2) የመስክ ላይ ስልጠናና ክትትል፣ (3) የማነቃቂያ አውደ ጥናት<br>2. (1) የመስክ ላይ ስልጠናና ክትትል፣ (2) የገበያ ጥናት ማካሄድ፣ (3) የሰብል ማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት<br>3. (1) የማነቃቂያ አውደ ጥናት፣ (2) የመስክ ላይ ስልጠና፣ (3) የገበያ ጥናት ማካሄድ<br>4. (1) የማነቃቂያ አውደ ጥናት. (2) የገበያ ጥናት ማካሄድ፣ (3) የመስክ ላይ ስልጠናና ክትትል | 4 | የሼፕ 4ቱ ደረጃዎች 1)ከአርሶ አደሮች ጋር ራዕይን መጋራት 2)የአርሶ አደሮችን ግንዛቤ ማሳደግ 3)አርሶ አደሮች በራሳቸው መወሰን ይችላሉ 4)አርሶ አደሮች ክህሎት ያገኛሉ |
| 4 | የማነቃቂያ ስብሰባ ዋነኛ አላማ ምንድን ነው? | 1. የተመረጡ አርሷደሮች የግብርና ክህሎታቸውና የማስተዳደር አቅማቸው በማዳበር በራስ መተማመን እንዲፈጥሩ ማስቻል<br>2. ሰብሎችን ለመምረጥ የገበያ ጥናት ማካሄድ | 1 | ሼፕ የአርሶ አደሮችን ነጻነትና ራስን በራስ ተማምኖ ግብርናን እንደቢዝነስ የማየት ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ይሰጣል።ሼፕ አርሶ አደሮች ከውጪ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3. የተመረጡ አርሶ አደሮች በሼፕ ስልጠና ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከተገኙ የዘርና ማዳበሪያ ድጎማ እንደሚደረግላቸው ቃል መግባት<br>4. የተመረጡ አርሷደሮች ወደ ቤታቸው ይዘዋቸው የሚሄዷቸው የተለያዩ የዳሰሳ ጥናት ፎርማቶችና የስልጠና መርጃዎችን ማከፋፈል | | ለሚሰጥ ለገንዘብም ሆነ ለቁሳቁስ ዕርዳታ ትኩረት እንዳይሰጡ ያበረታታል። |
| 5 | ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ የሼፕ አቀራረብ ስነ ፆታን ያማከለ ስራ እንደሚሰራ የሚያብራራው የትኛው ነው? | 1. በቤተስብ ደረጃ ውጤታማ የግብርና ስራ እንዲከናወን ለማስቻል ነው<br>2. በአካባቢና በክልል ደረጃ የሴቶችን የፖለቲካ ውክልናን ከፍ ለማድረግ ነው<br>3. የወንዶች የማምረት ክህሎትና የሴቶችን የግብይት ክህሎት ከፍ ለማድረግ ነው<br>4. ከአለም ዓቀፍ ድርጅቶች የፈንድ ድጋፍ ለመሳብ ነው | 1 | ሼፕ ስነ-ጾታ ውጤታማና ዘላቂነት ያለው የግብርና እድገት ለማረጋገጥና ግብርና እንደቢዝነስ ለማየት የሚስችልና ጠቃሚ መሆኑ ያምናል |
| 6 | በአትክልት አምራቾችና የገበያ ባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን የገበያ መረጃ አለመመጣጠን ችግር ለመቅረፍ የሼፕ አቀራረብ ምን ማድረግ አለበት? | 1. አርሷደሮችና የገበያ ባለድርሻ አካላትን በመካከላቸው ቀጥተኛ የገበያ መረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማገዝ<br>2. ለአርሷደሮች የገበያ ዋጋ መረጃ በስልክ መስጠት<br>3. ለአርሷደሮች የማምረት ክህሎት ማሳደጊያ ስልጠናዎችን መስጠት<br>4. ለአርሷደሮች አሳታፊ የመነሻ የዳሰሳ ጥናቶች ማካሄድ | 1 | ሼፕ አርሶ አደሮችና የግብይት አካላትን በቀጥታ በማገናኘት በመካከላቸው ያለውን የመረጃ ክፍተት እንዲያስወግዱ የሚያስችል ነው |
| 7 | ከማነቃቂያ ስብሰባ በኋላ ከተሳታፊ አርሷደሮች ከሚከተሉት ውስጥ የትኛውን ምላሽ ይጠብቃሉ? | 1. ‹‹ወደፊት አንዳንድ የመንግስት ድጎማዎችን መጠበቅ ስለሚያስችለን ተሳታፊ አርሶ አደር ተደርገን መመረጣችን ጥሩ ነው።;››<br>2. ‹‹የሼፕ አቀራረብ እንደ ማከማቻ ማዕከላት፣ ተሽከርካሪዎች ወይም የግብርና ማሽኖች የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማግኘት እንደሚያስችለን እንገነዘባለን።››<br>3. ‹‹ከሼፕ ስልጠናዎች በኋላ እራሳችንን በራሳችን የምንመራ አርሷደሮች የመሆን ኃላፊነት የእኛ እንደሆነ እንገነዘባለን።›› | 3 | ሼፕ የአርሶ አደሮችን አቅም በመገንባትና በራሳቸው ተማምነው ግብርና እንደቢዝነስ እንዲያዩ ማስቻል ነው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 4. ‹‹የሼፕ ስልጠናዎችን በስኬት ካጠናቀቅን የግብርና ኢንቨስትመንታችንን ለማሻሻል የሚያስችሉንን ብድሮች ማግኘት ስለምንችል እድለኞች ነን፡፡›› | | |
| 8 | ከሚከተሉት መካከል በሰብል ማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ዝግጅት ወቅት የአርሷደሮችን ግንዛቤ ለማሳደግ ተገቢው ዘዴ የትኛው ነው? | 1. አስፈጻሚዎች ጥቂት የተማሩ የቡድን መሪዎች ለቡድኑ ሁሉንም ነገር እንዲወስኑ መጠየቅ<br>2. አስፈጻሚዎች የዩኒቨርሲቲ የግብርና ሙያተኞችን አርሷደሮችን ሙያተኞቹ ባዘጋጁቸው የሰብል መዝሪያ የጊዜ ሰሌዳዎች መሰረት የተወሰኑ ሰብሎችን እንዲዘሩ እንዲያሳምኑላቸው መጋበዝ<br>3. አስፈጻሚዎች በአርሷደሮች መካከል የሚካሄዱ ውይይቶችን ማመቻቸት እና አርሷደሮችን በራሳቸው እንዲያቅዱ መፍቀድ<br>4. የአስፈጻሚዎች የሰብል መዝሪያ የጊዜ ሰሌዳ ረቂቅ በማዘጋጀት አርሷደሮችን ይህን እንዲተገብሩ መጠየቅ | 3 | የአርሶ አደሮችን ፍላጎት ለማነቃቃት በራሳቸው እንዲወስኑ ማስቻል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ይህም የስነልቦናዊ ፍላጎታቸውን በማሟላት ነጻነት እንዲሰማቸው ያደርጋል |
| 9 | ከሚከተሉት ውስጥ ከተመረጡ አርሷደሮች ጋር ለመስራት የገበያ ጥናት ከመካሄዱ በፊት መደረግ ስላለበት ተገቢ ቅድመ ዝግጅት የበለጠ የሚገልጸው የትኛው ነው? | 1. የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ስለገበያ ጉብኝት ልምድ ከሌላቸው የመጀመሪያ ደረጃ የገበያ ጥናት ለማካሄድ የገበያ ጥናት አማካሪ ሙያተኞች መቅጠር አለባቸው፡፡<br>2. የኤክስቴንሽን ሰራተኞች አርሷደሮችን ሳይይዙ ወደ የገበያ ቅድመ ጥናት መሄድ የለባቸውም፡፡<br>3. የኤክስቴንሽን ሰራተኞች የገበያ ጥናት ለማካሄድ የሳምንቱን ተገቢ ቀንና የቀኑን ተገቢ ሰዓት መምረጥ አለባቸው፡፡<br>4. የኤክስቴንሽን ሰራተኞች የገበያ ጥናት ያለ ምንም ችግር ለማካሄድ ከአርሷደር ቡድኖች መካከል የተሻለ ትምህርት ያላቸውን መምረጥ አለባቸው፡፡ | 3 | የገበያ ጥናት ማድረጊያ ቀንና ሰዓት ለአርሶ አደሮችና ለግብይት አካላት አመቺ መሆን አለበት፡፡ይህም በተገቢው ተወያይተው አስፈላጊው መረጃ እንዲለዋወጡ ያስችላል፡፡ |
| 10 | ከሚከተሉት መካከል የገበያ ጥናት በአምራቾችና ገዢዎች መካከል ያለውን ክፍተት እንደሚዘጋ ***ከግምት የማያስገባው*** የትኛው ነው? | 1. አርሷደር ሲናገር ‹‹ ከዚህ ቀደም ስለምርቴ የቆይታ ጊዜ አያሳስበኝም ነበር፡፡ከአሁን በኋላ በዚህ ጉዳይ መጠንቀቅ አለብኝ፡፡ በዚህም ገዢዬን ማስደሰት እችላለሁ፡፡›› | 3 | የገበያ ጥናት አንዱ ዓላማ አምራቾችና ገዢዎች ፍላጎታቸውን በተገቢው በመግለጽ በመካከላቸው መተማመንን መፍጠር ነው፡፡ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. ገዢ ሲናገር ‹‹በአካባቢው ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው ድንች የሚያመርቱ አርሷደሮች መኖራቸውን አላውቅም ነበር። ወደፊት ጥራት ያለው ድንች ከአካባቢ መግዛት በመቻሌ ደስተኛ ነኝ››<br>3. ጅምላ ነጋዴ ሲናገር ‹‹ከአነስተኛ አርሷደሮች ቲማቲም ምርት መግዛት የጥራት ደረጃ ስለማያስተማምን ከሰፋፊ እርሻዎች የሚመረቱ ቲማቲሞችንመግዛት ይሻለኛል››<br>4. አገናኝ ደላላ ሲናገር ‹‹የአርሷደሮች ቡድኖች በቂ የድንች ምርት (አንድ አይሱዙ የሚሞላ) እንዳላቸው ቃል ስለገቡልኝ ማጓጓዣ አዘጋጅቼ ማሳቸው ድረስ እሄዳለሁ ›› | | |
| 11 | ከሚከተሉት ውስጥ የሼፐን የገበያ ጥናት የማይገልጸው የትኛው አረፍተ ነገር ነው? | 1. አርሷደሮች የገበያ ጥናት በሚያካሂዱበት ወቅት ገዢዎች የትኛውን ዝርያ እንደሚመርጡ፤ቀጥታ ከማሳቸው ሊገዟቸው ስለመቻላቸውና በምን ያህል መጠን የመሳሰሉ ቀላል ጥያቄዎችን በመጠየቅ የገበያ ጥናት እንዲያካሂዱ ይመከራሉ።<br>2. አርሷደሮች የገበያ ጥናት የሚያካሄዱት የአትክልት ምርታቸውን ከሰበሰቡ በኋላ መሆን አለበት።<br>3. አርሷደሮች ሌሎች የገበያ እድሎችን መቃኘት አለባቸው። ለምሳሌ፡- ዩኒቨርሲቲዎች፣ ማረሚያ ቤቶች፣ አዳሪ ትምህርት ቤቶች ወይም የአካባቢ ልዩ ዝግጅቶችን (ጾም፣ ሀዘን፤ሰርግ) ወዘተ…<br>4. አርሷደሮች የመደራደር አቅም ለመፍጠርና፤በቂ ምርት ማቅረብ እንዲችሉ ያገኙትን የገበያ መረጃ ለሌሎች ቡድኑ አባላት እንዲያካፍሉ መበረታታት አለባቸው። | 2 | አርሶ አደሮች የገበያ ጥናት ማድረግ ያለባቸው የሚያመርቱትን ሰብል ከመወሰናቸውና ሰብል ከመሰብሰባቸው በፊት መሆን አለበት።ሰብል ከሰበሰቡ በኋላ ገበያ መፈለግ እንዳይበላሽባቸው ቶሎ መሸጥ ስለሚፈልጉ የመደራደር ዓቅማቸው ይቀንሳል። |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 12 | የተመረጡ አርሶ አደሮች የገበያ ጥናት ልምምድ ካካሄዱ በኋላ የሼፕ አስፈጻሚዎች ከአርሶ አደሮቹ መስማት ያለባቸው የትኛው ነው? | 1. ‹‹የገበያ ጥናት በመንግስት አካላት ላይ ጥገኛ መሆን ሳያስፈልገን በራሳችን ማካሄድ የምንችለው ነው››<br>2. ‹‹በማዕከላዊ ገበያ ላይ እየተሸጡ ስላሉ የበለጠ ትርፋማ ስለሚያደርጉ ሰብሎች ማጥናት የበለጠ ጠቃሚ ነው።››<br>3. ‹‹የገበያ ጥናቱ ሌሎች አርሷደሮች ማለትም ተፎካካሪዎቹ ይህንን ጠቃሚ መረጃ እንዳያውቁ ለማድረግ በግለሰብ ደረጃ በሚስጥር መካሄድ አለበት።››<br>4. ‹‹የገበያ ጥናቱ በጣም ጠቃሚ በመሆኑ የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ቀጣዩን የገበያ ጥናት ቢያመቻቹልን ይመረጣል።›› | 1 | የኤክስቴንሽን ባለሞያ አርሶ አደሮች በጋራ ገበያ የማጥናትና መረጃ እንዲለዋወጡ ያበረታታል ያግዛል እንጂ እነሱን ተክቶ ገበያ አያጠናም |
| 13 | አርሷደሮች የገበያ ጥናት በሚያካሂዱበት ወቅት ምን አይነት መረጃ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል? እባክዎ ከተዘረዘሩት ውስጥ ***ትክክለኛ ያልሆነውን*** ይምረጡ። | 1. ተመራጭ የምርት አይነቶች፣ ምርት በከፍተኛ ደረጃ የሚፈለግበት ጊዜ (ወራት)፣ የክፍያ ሁኔታ (በአቅርቦት በካሽ፣ ከአቅርቦት ሁለት ሳምንት በኋላ)<br>2. የገዥዎች ስም፣ አድራሻ፣የገበያ ተግዳሮቶች፣ገዢዎች ምርቱን ከአርሷደሮች የመግዛት ፍላጎት<br>3. የገዥዎች ስም፣ የገዥዎች የአትክልት ምርጫዎች አይነት፣ የአንዱ መለኪያ መግዣ ዋጋ፣ የገዥዎች የቤተሰብ አባላት ብዛት<br>4. የአትክልት አይነት፣ ተመራጭ ዝርያ፣ መጠን (ኪግ) እና የአቅርቦት ድግግሞሽ (በየቀኑ/በሳምንት) ፣ የክፍያ ሁኔታ (በገንዘብ፣ በቼክ፣ በባንክ ሀዋላ) | 3 | በገበያ ጥናት ወቅት ገዢ ስለሚወደው የአትክልት ዓይነትና ስለቤተሰብ ቁጥር መረጃ መጠየቅ አስፈላጊ አይደለም |
| 14 | የገበያ ጥናት ከተጠናቀቀ በኋላ የአርሷደሮች ተወካዮች የስራ ድርሻዎች ምንድን ናቸው? | 1. የገበያ ጥናት ትግበራ ሪፖርት ጽፎ ለመንግስት መ/ቤቶች ማቅረብ<br>2. የሰበሰቡትን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ተመልሰው መረጃው ወደሰበሰቡበት ነጋዴዎች መሄድ | 4 | የገበያ ጥናቱን ያደረጉ ተወካይ አርሶ አደሮች ስለገበያ ጥናቱ ውጤት ለሌሎች የቡድኑ አባላት መረጃ እንዲሰጡ የፕሮጀክቱ አስፈጻሚዎች ማመቻቸት አለባቸው |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 3. የገበያ ዋጋ መረጃን ከመንግስት ድረገጽ ላይ በማረጋገጥ እና የዋጋ ልዩነቶች ካሉ ለመንግስት መ/ቤቶች ሪፖርት ማቅረብ<br>4. የቡድን ስብሰባ በማዘጋጀት በገበያ ጥናት ወቅት የሰበሰቧቸውን መረጃዎች ለሌሎች የአርሶ አደር ቡድን አባላት ማካፈል | | |
| 15 | ከተዘረዘሩት ውስጥ ስለሰብል ማምረቻ የጊዜ ሰሌዳ ልምምድ ዓላማን የማይገልጸው የትኛው ነው? እባክዎ ትክክለኛ ያልሆነውን ይምረጡ። | 1. የሰብል አመራረት የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት አርሷደሮች የመረጧቸውን ሰብሎች በማምረት ትርፍማ ለመሆን ምን ያክል ገንዘብ እንደሚያስፈልጋቸው ማወቅ ይችላሉ።<br>2. የሰብል የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት አርሷደሮች በገበያ ፍላጎት ላይ ተመስርተው የሰብል ማምረት እቅድ ለማዘጋጀት ያስችላቸዋል።<br>3. አርሷደሮች የኤክስቴንሽን ባለሞያዎች የሚነግራቸውን የጊዜ ሰሌዳ መከተል አለባቸው<br>4. የሰብል ጊዜ ሰsሌዳ በሚያዘጋጁበት ጊዜ አርሷደሮች በተጨማሪም በሰብል የገዜ ሰሌዳ ላይ የተዘረዘሩ ተጨማሪ መሰረታዊ የአመራረት መረጃ ያገኛሉ። | 3 | የሼፕ አቀራረብ የርሶ አደሮችን ፍላጎት መሰርት ስለሚያደርግ አርሶ አደሮች በራሳቸው መወሰን አለባቸው።ይህም አርሶ አደሮች ነጻነት እንዲሰማቸው ያደርጋል |
| 16 | ***በመደበኛነት***፡- የመስክ ላይ ስልጠና መስጠት ያለበት ማን ነው? | 1. የኤክስቴንሽን ሰራተኞች<br>2. የማዕከላዊ መንግስት ሰራተኞች<br>3. የዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች<br>4. የግብርና ምርምር ተቋማት ሙያተኞች | 1 | የኤክስቴንሽን ባለሞያ ለአርሶ አደሮች ቀረቤታ ስላላቸው የመስክ ስልጠና መሰጠት ያለበት በነሱ ነው |
| 17 | የተመረጡ አርሷደሮች የመስክ ስልጠና ላይ ለመሳተፍ በጣም ስራ እንደሚበዛባቸው ይናገራሉ። እርሶ ምን ያደርጋሉ ወይም ምን ማድረግ አለብዎት? | 1. ለአርሷደሮች አበልና ምሳ አዘጋጃለሁ<br>2. ከተመረጡ አርሷደሮች ውጪ በአጎራባች የሚገኙ አርሷደሮችን በስልጠናው ላይ እንዲሳተፉ አደርጋለሁ<br>3. ስልጠናውን ከአርሷደሮች የማምረቻ ጊዜ ጋር በማገናዘብና ከአርሷደሮች ጋር በመመካከር አዘጋጃለሁ<br>4. ቤት ለቤት በመዘዋወር ላገኘሁት ሰው ስልጠናውን እሰጣለሁ | 3 | የመስክ ስልጠና መዘጋጀት ያለበት አብዛኛው አርሶ አደር መገኘት በሚችሉበት ቀንና ሰዓት መሆን አለበት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 18 | ክትትልና ግምገማ የማድረግ ዋነኛው አላማ ምንድን ነው? | 1. አርሷደሮችን በመንግስት በአካባቢው እንዲያመርቱ የተነገራቸውን ሰብሎች በበቂ ሁኔታ ስለማምረታቸው የአካባቢው አስፈጻሚዎች ተገቢው ግፊት ስለማድረጋቸው መከታተል<br>2. አርሷደሮች የተማሯቸውን ቴክኒኮችና ዕውቀት መተግበራቸውን ለማረጋገጥ<br>3. አርሷደሮች በግብርና ስራቸው ላይ የሚያውሉት ብድር ከገንዘብ ተቋማት ማግኘታቸውን ማረጋገጥ<br>4. በዋና ዋና የማሳ ሰብሎች ምርት ላይ አሀዛዊ መረጃ ማገግኘት | 2 | ክትትልና ግምገማ አርሶ አደሮች በሼፕ ስልጠና ያገኙትን የቴክኒክ ዕውቀትና ክህሎት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ያበረታታቸዋል |
| 19 | ከሚከተሉት ውስጥ የኤክስቴንሽን ሰራተኛ ለተመረጡ አርሷደሮች የሥርዓተ-ጾታ ስልጠና በሚያዘጋጅበት ወቅት **ሊኖረው የማይገባ አመለካከት** የትኛው ነው? እባክዎ ***ትክክል ያልሆነውን*** ይምረጡ | 1. ሴትና ወንድ አርሷደሮችን እርስ በርሳቸው ከስርአተ ጾታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግዳሮቶችን በመወያየት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ማበረታታት።<br>2. ሴትና ወንድ አርሷደሮች ከስርአተ-ጾታ አንጻር ለሚታዩ ችግሮች መፍትሄ የሚፈልጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት<br>3. ስለ ሥርአተ ጾታ ሚናዎችና በባልና ሚስት መካከል በጋራ ውሳኔ ሰጪነት የተመለከቱ አንዳንድ ጥሩ ልምዶችና የስኬት ታሪኮችን ማካፈል<br>4. አርሷደሮችን ለተወሰኑ ከስርአተ-ጾታ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ጉዳዮች ማን ኃላፊነት መሸከም እንዳለበት የመወቃቀሻ መድረክ መክፈት። | 4 | በስነ-ጾታ ስልጠና ወቅት እርስ በርስ የመተቻቸት ሳይሆን ጥሩ የውይይት መንፈስ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል |
| 20 | ከሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ የኤክስቴንሽን ሰራተኛ በመደበኛ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ግንኙነት በትክክል የማይገልጸው የትኛው ነው።? እባክዎ ትክክለኛ ያልሆነውን ይምረጡ። | 1. ከግብርና ሚኒስቴር በይፋ የተገለጹ የገበያ መረጃዎችን (የአትክልት ዋጋ) መረጃ ማካፈል ጠቃሚ ነው | 1 | አርሶ አደሮችና የኤክስቴንሽን ባለሞያዎች ሁልጊዜ ከሚመለከተው አካል ብቻ የገበያ መረጃ መጠበቅ የለባቸውም። በተከታታይ የገበያ ጥናት ማድረግ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | 2. ከአርሷደሮች ጋር ስለ ገበያ መረጃ መወያየትና አርሶ አደሮች ከሰብል ስብሰባ በፊት የገበያ ጥናት እንዲያካሂዱ ማበረታታት አስፈላጊ ነው<br>3. አርሷደሮችን በተቻለ መጠን አስቀድመው ከአቅራቢዎች/ገዢዎች ጋር በስልክ ወይም የገበያ ጉብኝት በማድረግ ግንኙነት እንዲጀምሩ መምከር አስፈላጊ ነው<br>4. ከተረጋገጡ የዘር አቅራቢዎች በጋራ የግብአት ግዢዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ሲሆን ይህም የአርሷሮችን የምርት ጥራት በማሳደግ የማምረቻ ወጪያቸውን ይቀንሳል። | | አለባቸው።ምክንያቱም የገበያ ዋጋ ከጊዜ ጊዜና ከቦታ ቦታ ስለሚለዋወጥ ነው |